ቁጥር፡ -----
Ref: አብክመጤ/1012/18
ቀን፡ -----
Date: 08/12/2018

አብክመ ጤና ቢሮ
AMHARA HEALTH BUREAU

- ለሁሉም ዞን/ከተማ አስተዳደር ጤና መምሪያዎች
- ለሁሉም ወረዳ/ከተማ አስተዳደር ጤና ፅ/ቤቶች
- ለሁሉም ሆስፒታሎች፤
- ለሁሉም የደም ባንክ አገልግሎት፤
- ለሁሉም የኦክስጅን ማምረቻ እና ማከፋፈያ ማዕከላት፤
- ለሁሉም የአካል ድጋፍ ታህድሶ አገልገሎት ማዕከላት

በያሉበት

ጉዳዩ፡ <u>የተሻሻለ የጤናው ዘርፍ የመንግስት ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የሚፈቀድበት ሁኔታ እና ክፍያ ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ ስለማሰወቅ።</u>

ከላይ በጉዳዩ እንደተገለፀው የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሐምሌ 18/2018 ዓ.ም ባካሄደው 7ኛ ዙር 1ኛ ዓመት የስራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ስብሰባ በአብክመ በመንግስት የጤና ተቋማት የሚሰሩ የጤናው ዘርፍ ሰራተኞች የተሻሻለ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የሚፈቀድበት ሁኔታ እና ክፍያ ለመወሰን መመሪያ ቁጥር ፮፰/፪ሺ፲፰ አውጥቷል።

ስለሆነም የተሻሻለዉ መመሪያ ከሀምሌ1/2018 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ እንዲሁም ከመስከረም 1/2019 ዓ.ም ጀምሮ በስታንዳርዱ መሰረት የተሰራው ስምሪት ተግባራዊ እንዲደረግ ---ገፅ አባሪ አያይዘን የላክን ሲሆን መስተዳድር ምክር ቤቱ የወሰነዉን ዉሳኔ እና የተቀመጠዉን ስምሪት በመጣስ የሚተገብር ሀላፊ ወይም ባለሙያ ካለ አስፈላጊዉ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን አሳስባለሁ ::

ጤና ለሁሉም

ግልባጭ//

- ለጤና ፋይናንስ እና ጤና መድህን ዳይሬክቶሬት
- ለህክምና እና ታህድሶ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

የአማራ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ ስለከረም መንግስቱ ይማም አብክመ ጤና ቢሮ ኃላፊ

ባ/ዳር

ፃራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

Office of the Head of Government in
The Amhara National Regional State

ቁጥር አብክመ/ዐ 1532/ወጽ-ኦ-1
ቀን 26/12/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ገንዘብ ቢሮ
ለአብክመ ጤና ቢሮ
ባህር ዳር፣

ጉዳዩ፡- **የመስተዳድር ምክር ቤቱን ውሳኔ ስለማሳወቅ፣**

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሐምሌ18 ቀን 2018 ዓ.ም ባካሄደው 7ኛ ዙር 1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ስብሰባ በአብክመ በመንግስት የጤና ተቋማት የሚሰሩ የጤና ዘርፍ ሠራተኞች የተሻሻለው የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የሚፈቀድበት ሁኔታ እና ክፍያ ለመወሰን የወጣ ረቂቅ መመሪያ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፉ ይታወሳል።

በመሆኑም መስተዳድር ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ በስፋት ተወያይቶ፣ በመመሪያው መሻሻል ላይ በመስማማት መመሪያውን ተቀብሎ ያፀደቀው ሲሆን በዚህም መሰረት፡- መመሪያው በመስተዳድር ም/ቤቱ ተርቦ ከፀደቀበት ከሐምሌ ወር 2018 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን እና ውዝፍ ክፍያን እንደማያስተናግድ የወሰነ መሆኑን እያሳውቅሁ፣ ለአፈፃፀም ያመች ዘንድ መመሪያ ቁጥር ፳፰/፪ሺ፲፰ ዓ/ም ባለ 8 ገጽ ተያይዞ ተልኳል።

ከሰላምታ ጋር

አረጋ ከበደ ለጋስ
ርዕሰ መስተዳደር

ግልባጭ//

- ለምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ /ያለአባሪ/
- ለጽ/ቤቱ ኃላፊ /ያለ አባሪ/
- ለካቢኔ ሴክሬታሪያት ዳይሬክቶሬት

ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፣

☎ + 251 058 220 0924/499 ✉ 312 + 251 058 220 1068/1660
E-mail :amrspmofo@gmail.com website www.amhararcg.gov.et

መመሪያ ቁጥር ፮፮/፪ሺ፲፮ ዓ.ም.

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በመንግስት የጤና ተቋማት የሚሰሩ የጤና ዘርፍ ሠራተኞች የተሻሻለዉ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የሚፈቀድበት ሁኔታ እና ክፍያ ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ

የጤና ዘርፍ ስራ ከሰዉ ሕይወት ጋር የተያያዘ እና አገልግሎቱም በስራ ቀናት፤ በሳምንቱ መጨረሻ የዕረፍት ቀናት እንዲሁም የሕዝብ በዓላት በሆኑ ቀናት ጭምር ሳይቀራረጥ ለሃያ አራት ሰዓታት የሚሰጥ በመሆኑ ከመንግስት የስራ ሰዓት ዉጭ ለሚሰራ ሥራ ተመድበዉ ለሚሰሩ የጤና ዘርፍ ሰራተኞች ወጥ የሆነ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ መክፈል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከሚታየዉ የአገልግሎት ፈላጊ ህዝብ ብዛትና ይኸው ከሚፈጥረዉ የሥራ ጫና አንፃር የጤናው ዘርፍ ሰራተኞች ኃላፊነትና ግዴታቸውን በሙሉ ተነሳሽነት፣ ሙያዊ ብቃትና የተሟላ ሥነ ምግባር እንዲወጡና ተረጋግተው እንዲሰሩ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

በሀገር አቀፍ ደረጃ የመንግስት የጤና ተቋማት ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ሥራ የሚፈቀድበት ሁኔታ እና ክፍያ ለመወሰን በፌዴራል የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የወጣዉን መመሪያ ቁጥር ፩፻፲፱/፪ሺ፲፮ ዓ.ም ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም አድርጎ መተግበር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፰ ንዑስ አንቀጽ ፩ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በመንግስት የጤና ተቋማት የሚሰሩ የጤና ዘርፍ ሰራተኞች የተሻሻለዉ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የሚፈቀድበት ሁኔታ እና ክፍያ መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ ቁጥር ፮፮/፪ሺ፲፮ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

፩) "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሲቪል ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ ነው፤

፪) "የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ" ማለት ከመንግሥት መደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ በሆነ ሌሊት ወይም ቅዳሜ እና እሁድ ተናት ወይም የህዝብ በዓላት ተን በመንግስት የጤና ተቋማት ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጥ ለተመደበ የጤና ዘርፍ ሰራተኛ እንዲከፈል በዚህ መመሪያ የተወሰነው የክፍያ ዓይነት ነው፤

፫) "የትርፍ ሰዓት ሥራ" ማለት ማንኛውም የክልሉ መንግሥት የጤና ተቋም የ24 ሰዓት አገልግሎት ለመስጠት ይቻለው ዘንድ የተለያየ ሙያ ያላቸው የጤና ዘርፍ የመንግስት ሰራተኞች ፕሮግራም እየወጣላቸው መደበኛ ከሆነው የመንግሥት ሥራ ሠዓት ውጭ ህብረተሰቡን እንዲያገለግሉ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፤

፬) "የትርፍ ሰዓት ሥራ ተመጻቢ" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የትርፍ ሰዓት ሥራ ተመጻቢ ሆኖ እንዲያገለግል የተመደበ የጤና ዘርፍ የመንግስት ሰራተኛ እንዲሠራ በተመደበባቸው ሰዓታት ሁሉ በአንድ የመንግስት ጤና ተቋም ውስጥ ሙሉ ጊዜውን አገልግሎት እንዲሰጥ የሚገደድበት አሠራር ነው፤

፭) "ተጠባባቂ ተረኛ" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት እንዲያገለግል የተመደበ ባለሙያ ሙሉ ጊዜውን በተመደበበት ተቋም ትጥር ግቢ ማሳለፍ ሳያስፈልገው የእሱ ልዩ እገዛ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ካለበት አካባቢ እየተጠራ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚደረግበት አሠራር ነው፤

፮) "የጤና ዘርፍ የመንግስት ሰራተኛ" ማለት በጤናው ዘርፍ በጤና ባለሙያነት ወይም በአስተዳደር ሰራተኝነት በመንግስት የጤና ተቋማት ውስጥ በቋሚነት ወይም በኮንትራት ተተጥሮ የሚሰራ ማንኛውም ሰራተኛ ነው፤

፯) "የጤና ተቋም" ማለት በክልሉ መንግስት የተቋቋሙ የመንግስት ሆስፒታሎች፤ አከስጅን ፕላንቲሽን ማምረቻና ማከፋፈያ፤ ደም ባንኮች፤ የአካል ድጋፍ እና ተሀድሶ ማዕከላት፤ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፤ ወረዳዎችአስተሞች የሚያስተዳድሯቸው ጤና ጣቢያዎች እና ጤና ኪላምችን ያጠቃልላል፤

፰) "መደበኛ የስራ ሰዓት" ማለት በክልሉ መንግሥት በሕግ የተወሰነዉ መደበኛ የሥራ ሰዓት ነዉ፤

፱) "መደበኛ ደመወዝ" ማለት በአንድ የስራ ደረጃ ለተመደቡ ስራዎች የተወሰነ መነሻ ክፍያ ወይም የእርከን ክፍያ ሲሆን ለኑሮ አስቸጋሪ በሆኑ የበረሃ እና የውርጭ አካባቢዎች የተፈቀደ የበረሃ ወይም የውርጭ አበል ክፍያን አይጨምርም፤

፲) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፩) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አገላለጽ የሴት ጾታንም ይጨምራል።

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የመንግስት የጤና ተቋማትና የጤና ዘርፍ የመንግስት ሰራተኛ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

፬. ዓላማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩) የጤናው ዘርፍ የመንግስት ሰራተኞች ተነቃቅተውና ተረጋግተው እንዲሠሩ ማስቻል፤

፪) ጥራቱን የጠበቀ፣ ቀልጣፋ እና የታካሚውን ፍላጎት ያማከለ የህክምና አገልግሎት ለህብረተሰቡ የሚሰጥበትን ስልት ውጤታማ ማድረግ፤

፫) በዘርፉ ያለውን ውስን የሰው ኃይል በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

፬) ስታንዳርድ በማዘጋጀት እና በመተግበር በጤና ተቋማት ውስጥ የሚታየውን የአሰራር ችግር ማስወገድና የመልካም አስተዳደር ችግርን ማቃለል ነዉ።

ክፍል ሁለት

የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ አመዳደብ ስታንዳርድ፣ የሚከፈልበት ሁኔታዎችና የክፍያ መጠን

፭. ስለትርፉ ሰዓት ስራ አመዳደብ ስታንዳርድ

፩) በመንግስት ተቋማት የሚያገለግሉ የጤናው ዘርፍ የመንግስት ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ አመዳደብና የመ.ያ ዓይነት እንዲሁም ብዛት በተመለከተ ከመደበኛ የመንግስት የስራ ሰዓት በተጨማሪ በሌሎች የስራ ሰዓት የሚሰጡ አገልግሎቶችን መሰረት በማድረግ በጤና ቢሮ የሚወሰን ይሆናል፤

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የመሰረታዊ ጤና ኪላምች የትርፍ ሰዓት ሥራ አመዳደብ እና አሰራር በጤና ጣቢያው ስር ይሆናል፤

ሸ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተመለከቱትን ታሳቢ ያደረገ የትርፍ ሰዓት ስራ ስምሪት ይሰጣል።

፮. የትርፍ ሰዓት ስራ ክፍያ ስለሚከፈልባቸው ሁኔታዎች

በዚህ መመሪያ መሠረት የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ ሊከፈል የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ይሆናል፦

፩) በማናቸውም ጊዜና ሁኔታ ሊቋረጥ የማይችል የጤና አገልግሎት ሲኖር፤

፪) በህዝብ በዓላት ቀን ወይም ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ በሌሊት ወይም ቅዳሜና እሁድ ቀናት በትርፍ ሰዓት ሥራ መሠጠት ያለበት የጤና አገልግሎት መኖሩ ሲረጋገጥ።

፯. በተረኝነትና በተጠባባቂ ተረኝነት የሚሰራ የመንግስት የጤና ዘርፍ ሰራተኛ መብትና ግዴታ

፩) ማንኛውም ባለሙያ በወጣው የተረኝነትና የተጠባባቂ ተረኝነት ፕሮግራም መሰረት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት የመወጣት ግዴታ አለበት፤

፪) ማንኛውም በተረኝነት ወይም በተጠባባቂ ተረኝነት የተመደበ ባለሙያ የሰጠውን አገልግሎት በተቋሙ ስታንዳርድ መሰረት ያከናወነውን ተግባራት የመመዝገብ ግዴታ አለበት፤

፫) ማንኛውም በተረኝነት ወይም በተጠባባቂ ተረኝነት የተመደበ ባለሙያ ስራ ሲጀምር እና ጨርሶ ሲወጣ የስራ ርክክብ ማድረግ ግዴታ አለበት፤

፬) የትርፍ ሰዓት ሥራ አገልግሎት የሰጠ ሰራተኛ በዚህ መመሪያ መሰረት የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ እንዲፈጸምለት የመጠየቅ መብት አለው።

፰. የትርፍ ሰዓት ስራ አመዳደብ እና አከፋፈል ሁኔታ

፩) በተቋሙ ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ የጤናው ዘርፍ የመንግስት ሰራተኞች እና በተለያየ ደረጃ ያሉ ኃላፊዎች ባየስራ ምድባቸው በትርፍ ሰዓት ሥራ ሊመደቡ ይችላሉ፤

፪) አመዳደቡ በስታንዳርድ የሚመራ የስራ ጫናን እና ውጤትን መሰረት ያደረገ ይሆናል፤

፫) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ እና ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋማት ለደንበኞች የሚሰጡትን አገልግሎት ሪፖርትን ከጤናው ሴክተር የመረጃ ቋት በመውሰድ እና በመተንተን ይሆናል፤

፬) በየወቅቱ አገልግሎት እየሰፋ እና እየተሻሻለ ሲሄድ ወይም አዳዲስ አገልግሎቶች እየሰፉ ሲሄዱ የትርፍ ሰዓት ሥራ ተመዳቢዎች ቁጥር ሊጨምር የሚችለው በጀት መኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

፯. ትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ መጠንና አሰላል

፩) በዚህ መመሪያ መሰረት በትርፍ ሰዓት ሥራ ተመድቦ የሚሰራ የጤናዉ ዘርፍ የመንግስት ሰራተኛ በወር የሚያገኘው መደበኛ ደመወዝ ለ30 ቀናት ሲካፈል በአንድ ቀን የሚያገኘው ደመወዝ እንዲሁም በቀን የሚያገኘው ደመወዝ ደግሞ ለ8 ሰዓት ሲካፈል በአንድ ሰዓት የሚከፈለውን ደመወዝ ይሰጣል፤

፪) በዚህ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ መሰረት በትርፍ ሰዓት ሥራ ተመድቦ የሚሰራ የጤናዉ ዘርፍ የመንግስት ሰራተኛ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ አበል የሚሰላዉ እንደሚከተለዉ ይሆናል፡-

ሀ) በስራ ቀናት ከምሽቱ 12:00 እስከ ምሽቱ 4:00 ሰዓት ለሚሰራዉ የትርፍ ሰዓት ሥራ ለመደበኛዉ ስራ በሰዓት የሚከፈለዉ ደመወዝ በ1.25 ተባዝቶ ይከፈላል፤

ለ) በስራ ቀናት ከምሽቱ 4:00 እስከ ንጋቱ 12:00 የሚሰራ የትርፍ ሰዓት ሥራ በሰዓት የሚከፈለዉ ደመወዝ በ1.5 ተባዝቶ ይከፈላል፤

ሐ) በሳምንቱ የዕረፍት ቀናት ማለትም ቅዳሜና እሁድ ለሚሰራዉ የትርፍ ሰዓት ሥራ በሰዓት የሚከፈለዉ ደመወዝ በ2 ተባዝቶ ይከፈላል፤

መ) በህዝብ የበዓል ቀናት የሚሰራ የትርፍ ሰዓት ሥራ በሰዓት የሚከፈለዉ ደመወዝ በ2.5 ተባዝቶ ይከፈላል፤

ሠ) ከቀኑ 11:30 እስከ ምሽቱ 12:00 እና ከንጋቱ 12:00 እስከ ጠዋቱ 2:30 የሚሰራ የትርፍ ሰዓት ሥራ በሰዓት የሚከፈለዉ ደመወዝ በ1 ተባዝቶ ይከፈላል፤

፫) የህዝብ በዓል ቀን እሁድ እና ቅዳሜ በሚሆንበት ጊዜ የሚከፈለው በህዝባ በዓል ቀን አሰላል መሰረት ነው፤

፬) ከመደበኛ ደመወዝ የሚገኝ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ ለኑሮ አስቸጋሪ በሆኑ የበረሃ እና የውርጭ አካባቢዎች የተፈቀደ የበረሃ ወይም የውርጭ አበል ክፍያ ተግባራዊ ይደረጋል፤

፭) ማንኛውም በትርፍ ሰዓት ሥራ ተመዳቢ ባለሙያ ያከናወነውን የስራ ውጤት በዕለቱ ለአገልግሎት ጥራት ቁጥጥር ክፍል ሪፖርት ማድረግ የሚኖርበት ሲሆን ይህ ባልሆነበት ሁኔታ በትርፍ ሰዓት ሥራ ተመድቦ ቢሰራ እንኳን ክፍያ መፈፀም አይቻልም::

፲. በተጠባባቂ ተረኝነት ስለሚመደቡ የጤና ሙያተኞች መብትና ግዴታ፤

፩) በትርፍ ሰዓት ሥራ እንዲያገለግሉ የሚመደቡ የጤና ሙያተኞች በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፱ መሠረት ሙሉ አበል ይከፈላቸዋል፤

፪) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ /፩/ የተጠቀሰዉ ቢኖርም በሥራ ቀን በሚመደቡበት ጊዜና ተጠባባቂ ሁኖ ተመድቦ ካልተፈለገ 30% ይከፈለዋል፤ሙሉ አገልግሎት ከሠጠ ሙሉ ይከፈለዋል::

፲፭. የትርፍ ሰዓት ስራ ክፍያ ከግብር ነፃ ስለመሆኑ

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚከፈል የትርፍ ሰዓት ስራ ክፍያ የሥራ ግብር አይከፈልበትም።

ክፍል ሦስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፮. ስለኃላፊነትና ተጠያቂነት

፩) ከዚህ መመሪያ ውጭ የሚፈፀም ማናቸውም የትርፍ ሰዓት ስራ ክፍያ ሕጋዊ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ይሆናል፤

፪) ማንኛውም በትርፍ ሰዓት ሥራ የተመደበ የጤናዉ ዘርፍ ሰራተኛ በተመደበበት ቦታ መገኘት ያለበት ሲሆን ከተመደበ በኋላ አቋርጦ መጥፋት፣ በክፍሉ ዉስጥ የመኝታ አልጋ ማስገባት ክልክል ነዉ፤

፫) የትርፍ ሰዓት ስራ ክፍያዉ ሰዓትን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የተመደበ ኃላፊ ወይም ባለሙያ በተቋሙ ከተገኘበት/ከሰራበት ጊዜ በላይ ክፍያ ጠይቆ የወሰደ እና ይህንኑ ክፍያ የመዘገበና ያረጋገጠ ኃላፊ በሕጉ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፤

፬) በትርፍ ሰዓት ሥራ ተመድቦ በተደጋጋሚ ጊዜ የደንበኛ ቅሬታ የቀረበበት የጤናዉ ዘርፍ ባለሙያ ወይም ስራው የሚመለከተው የአስተዳደር ሰራተኛ በትርፍ ሰዓት ሥራ እንዳይመደብ ሊወሰንበት የሚችል ሲሆን በተጨማሪም በዲሲፕሊን እዲጠየቅ ይደረጋል፤

፭) በትርፍ ሰዓት ሥራ የተመደበ የጤናዉ ዘርፍ ባለሙያ ወይም ስራው የሚመለከተው የአስተዳደር ሰራተኛ ከትርፍ ሰዓት ሥራ በፊት በትርፍ ሰዓት ሥራ አለበኝ ወይም ከትርፍ ሰዓት ሥራ በኋላ በትርፍ ሰዓት ሥራ አገልግያለሁ በሚል ምክንያት ከመደበኛ ሥራዉ መቅረትም ሆነ መዘግየት አይችልም።

፲፯. ስለጤና ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

፩) አንድን የጤና ዘርፍ ሰራተኛ ሰራሱ ጤንነትም ይሁን ለሚሰጠው አገልግሎት ጥራት ለማስጠበቅ በአንድ ወር ውስጥ ከ212 ሰዓት በላይ የትርፍ ስራ ሰዓት ስራ እንዲሰሩ ማድረግ የለበትም፤

፪) በዚህ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የጤናው ዘርፍ ስራ ከሰው ህይወት ጋር የተያያዘ በመሆኑ አገልግሎቱ ሳይቆራረጥ ለ24/7 የሚሰጥ በመሆኑ አንዳንድ ልዩ ሙያዎች እና ተጨማሪ ሙያተኛ የማይገኝባቸው ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ አገልግሎት እንዳይቋረጥ ጤና ቢሮው እየወሰነ ሊስተናገድ ይችላል፤

ሸ) ተጨማሪ የትርፍ ሰዓት ስራ ተመዳቢ የሚያስፈልግ ሁኖ ከተገኘ የታካሚ ብዛትና ይኸው የሚያስከትለውን የሥራ ጫና መሠረት በማድረግ ጤና ቢሮው ሲፈቅድ ብቻ ተግባራዊ ይደረጋል፤

ቀ) ጤና ቢሮው ስለትርፍ ሰዓት ተመዳቢ ባለሙያ አገልግሎትን መሰረት ያደረገ ስታንዳርድ ያወጣል፤

በ) ጤና ቢሮው ስታንዳርድ በማዘጋጀት እና በመተግበር በጤና ተቋማት ውስጥ የሚታየውን የአሰራር እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት መፍትሄ ይሰጣል።

፲፬. የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ጤና ተቋማት እና የሆስፒታሎች ስልጣንና ተግባር

ሀ) ተጨማሪ የትርፍ ሰዓት ስራ ተመዳቢ የሚያስፈልግ ሁኖ ከተገኘ የታካሚ ብዛትና ይኸው የሚያስከትለውን የሥራ ጫና መሠረት በማድረግ በቦርድ አተገመገመ ለጤና ቢሮ ሪፖርት ያደርጋል፤

ለ) ጤና ቢሮ ተጨማሪ የትርፍ ሰዓት ሥራ ተመዳቢ ሲፈቅድ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ በጀት ያስፈቅዳል፤

ሐ) ጤና ቢሮ በሚፈቅደው የተመዳቢ ቁጥር መሰረት በጀት እንዲያገ ያደርጋል፤

መ) ጤና ቢሮዉ በፈቀደዉ ስታንዳርድ መሰረት እና በተፈቀደ በጀት ባለሙያዎችን መድቦ ያሰራል፤ ይከታተላል፤ ክፍያ ይፈጽማል።

፲፭. የቢሮው ሥልጣንና ተግባር

ቢሮዉ፦

ሀ) መመሪያውን ማሻሻል ሲያስፈልግ የማሻሻያ ሃሳብ ለመስተዳድር ምክር ቤቱ አቅርቦ ያጸድቃል፤

ለ) በመመሪያዉ አፈጻጸም ዙሪያ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤ሲያስፈልግም ማብራሪያ ይሰጣል።

፲፮. ስለተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ሀ) በጤና ተቋማት ለሚያገለግሉ የጤና ተቋማት የተረኝነትና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ ቁጥር ፭/፪፻፲፯ ዓ.ም በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤

ለ) ከዚህ በፊት የተሳሰፉ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ አከፋፈል መወሰኛ ስርኩላር ደብዳቤዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፤

ሐ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች ቢኖሩም በዚህ መመሪያ መሠረት የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ከትርፍ ሰዓት ስራ ውጭ ተፈቅደው የነበሩ ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ባሉበት የሚቀጥሉ ይሆናል፤

፬) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሌላ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዘህ መመሪየ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

፲፯. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም.

አረጋ ከበደ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

	...ስ	ባለሙያ ለታካሚ ጥምርታ
	...ስ	1 ለ 1
	ጠቅላላ ሀኪም	1 ለ 5
	ኢመርጀንሲ እና ክሪቲካል ኬር ስፔሻሊስት	1 ለ10
...ማን ህክምና	ኢንተንሲቪስት/ፐልሞኖሎጅስት/ኢንተርኒስት	1 ለ10
	አንስተቲዮሎጅስት	1 ለ10
	ሌሎች ስፔሻሊስቶች	1 ለ10
	ፖርተር	1 ለ 50
	ገንዘብ ተቀባይ/ክሬዲት መገጋቢ	1 ለ 40
	ላውንደሪ	1 ለ 20
	የህመ.ማን ምግብ አስተናጋጅ/አዳይ	1 ለ 50
	የካርድ ክፍል ሰራተኞች የጤና መረጃ ባለሙ.ያ(ኤች አይ.ቲ)	1 ለ 40
	ፋርማሲ፤	1 ለ 30
	ክሊኒካል ፋርማሲ	1 ለ25 ለኮምፕረሲቭ፣130 ለጠቅላላ ፣1 35 ለመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል)
	ላብራቶሪ ፤	1 ለ 25
		ማይክሮ ባዮሎጀ ካልቸር እና የመድሀኒት ብግርነት ምርመራ ለሚሰራ 1 ሜዲካል ማይክሮ ባዮሎጅስት ይመደባል።
	ማገገሚያ ክፍል እና ሀይ ሪስክ እናቶች ክትትል(HDU)፤	1ለ 5
	ከወሊድ በኃላ ክትትል (ነርስ ወይም ሚድዋይፍ ወይም ጤና መኮነን)	1 ለ 20
	ሲኒየር ሀኪም	1 ለ 64
	ጠቅላላ ሀኪም	1 ለ 32
	ማዋለጃ ክፍል	1ለ 1
	ፅዳት ባለሙ.ያ	1 ለ 30
	ሴንተራል ስተራላይዘር	1ለ 30 ወላድ እና ቀዶ ህክምና ታካሚ
	ጥራት ቁጥጥር /የጤና አገልግሎት ማነቆ ተኮር ሪፎርም ትግበራ ቡድን	3 ለአጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፤2 ለጠቅላላ ሆስፒታል፤1 ለመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል
	ሰብ ስፔሻሊስት	1 ለ 50
	ስነ ደዌ ክፍል ባለሙ.ያ	በክፍል አንድ
	የስነ-ዓምሮ ተኝቶ ህክምና በጀመሩ ሆስፒታሎች	ሁለት
	ዲያሊስስ 1 ነርስ እና 1 ጠቅላላ ሀኪም	ለዲያሊስስ ሴንተር ብቻ
	ፊዚዉቴራፒ	1 ቅዳሜ እሁድ እና በረፍት ቀናት ብቻ(ለኮምፕረሲቭ ሆስፒታል)
	የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪ/ኢንቫይሮንመታል ሄልዝ	1 በጤና ተቋም ቅዳሜ እሁድ እና በባላት ቀን ብቻ
	ሁሉም አይነት ነርስ ከአይ.ሲ..ዩ እና ከድንገተኛ ክፍል ውጭ	1 ለ 8
ድንገተኛ ክፍል	ሁሉም አይነት ነርስ	1 ለ 5
	ኦፕሬሽን ክፍል(6 ባለሙ.ያ) በቴብል	2 ነርስ፤2 አንስቴዚያ አሲስታንት እና ቀዶ ህክምና የሚሰራው በአንድ ቴብል፤አንድ ቴብል 4 ይሰራል
ደረጃ አንድ ደም ባንክ (በሽታ	2 የላብራቶሪ ባለሙ.ያ አዳሪ እና አንድ ላብራቶሪ እና አንድ ነርስ/ጤና መኮነን ዋይ	
	5 አባላት ያሉት ተንቀሳቃሽ ቡድን ቅዳሜ እሁድ እና በህዝብ በዓላት ቀን ብቻ	ለቡድን ለ25 ዩኒት ደም አፈ.ፀፀም መሰረት የሚሰላ ሕሆናል

CamScanner

	ሪ ባለሙያ አዳሪ እና አንድ ሪ እና አንድ ነርስ/ጤና መኮንን ዋይ	
	ለባላት ያሉት ተንቀሳቃሽ ቡድን ቅዳሜ እሁድ እና በህዝብ በዓላት ቀን ብቻ	ለቡድን ለ25 ዩኒት ደም አፈሳሰም መሰረት የሚሰላ ሕሆናል
ላት ባንክ	1 የላብራቶሪ ባለሙያ አዳሪ እና አንድ ላብራቶሪ እና አንድ ነርስ/ጤና መኮንን ዋይ	
	5 አባላት ያሉት ተንቀሳቃሽ ቡድን ቅዳሜ እሁድ እና በህዝብ በዓላት ቀን ብቻ	ለቡድን ለ25 ዩኒት ደም አፈሳሰም መሰረት የሚሰላ ሕሆናል
የአካል ድጋፍ እና ትሀድሶ አገልግሎት		
አንድ ቡድን 4 አባላት የሚኖሩት	·1 ኦርቶፔዲክስ ቴክኒሽያን፤	
	·1 ረዳት ኦርቶፔዲክስ ቴክኒሽያን	
	·1 ፊዚዮቴራፒ፤	
	·1 ዕዳት	
ቅዳሜ፤እሁድ እና በህዝብ በአላት ቀን(ሐላፊው ን ጨምሮ 8 አባላት ያሉት ቡድን ይውላል)	አንድ ኃላፊ	
	አንድ አኮፔሽናል ቴራፒስት	
	አንድ ከራንች ሃንድልና ከራንች ቲፐስ ባለሙያ	
	አንድ ዊልቸር ባለሙያ	
	አንድ ዳታ ኢንኮደር	
	አንድ ካርድ ክፍል	
	አንድ ጋይዳንስ እና ካውንስለር	
	አንድ ንብረት ክፍል ይሆናሉ፡፡	
የአክሰጅን ማምረቻ እና ማከፋፈያ ማዕከላት	ሁለት ባዮሜዲክ ኢንጅነር እና አንድ የአለት ገንዘብ ሰብሳቢ ቅዳሜ እሁድ እና በህዝብ በአላት ቀን ብቻ	



		Different Category of Seniors for duty			
S/No	Category of Profession	Comprehensive S	General Hospital	Primary Hospital	ምርመራ
1	Gynecologist	2	1	1	ለደሴ እና ፈለገ ህይወት 3
2	Internist	2	1	1	
3	Surgeon	2	1	1	ለደሴ እና ፈለገ ህይወት 3
4	Pediatrician	2	1	1	
5	Orthopedic Surgeon	2	1	1	
6	Ophthalmologist	1	1	1	
7	Radiologist	2	1	1	
8	Psychiatrist	1	1	1	
9	Dermatologist	1	1	1	
10	Anesthesiologist	1	1	1	
11	Pathologist	1	1	1	
12	Oncologist	1	0	0	
13	Neurologist	1	0	0	
14	Urologist	1	0	0	
15	Neurosurgeon	1	0	0	
16	Intensivist	1	0	0	
17	Cardiologist	1	0	0	
18	ENT Specilist	1	0	0	
19	Maxillofacial Surgeon	1	0	0	
20	Pulmonlogist	1	0	0	
21	Other specialist and Sub pecialist	1	0	0	



		የጠቅላላ ሆስፒታሎች የትርፍ ሰዓት ስራ ተመጻዚዎች														
	የባለሙያ አይነት	አለም ከተማ	አይራ	ደባርቅ	መሀል ሜዳ	ሸጋው ሞጣ	ከሚሴ	ተፈራ ሀይሉ	አትስታ	ፍኖተ ሰላም	ቅዱስ ላሊበላ	መተማ	እንጂባራ	ቦሩ	ኮምቦልቻ	መካለ ሰላም
1	በሁሉም አይነት የሙያ እና የትምህርት ድጃ ያለ ነረስ	11	13	19	12	21	28	21	25	28	11	19	30	17	20	29
2	ሚድዋይፈሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	4	6	8	4	10	8	5	6	12	4	7	10	2	7	6
3	ጠቅላላ ሀኪም	3	4	4	4	4	5	4	5	5	4	4	5	4	4	5
4	የተቀናጀ የቀዶ ህክምና አፈሰር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
5	አንስዝያ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	3	2	2	3	2	2	2
6	ፋርማሲ(በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	3	3	4	2	5	5	4	4	5	2	4	5	4	4	5
7	ክሊኒካል ፋርማሲ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
8	ላቦራቶሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	3	3	4	3	5	6	5	5	6	3	5	7	5	5	5
9	የስነ ደዊ ላቦራቶሪ ምርመራ ክፍል	0	0	0	0	0	0	0	0	0	0	0	1	0	0	0
10	Radiology – Technician	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
11	Radiology – Technologist	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
12	ላይዘን(የማህበራዊ አገልግሎት ስራ ደርቦ ይራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
13	ካርድ ክፍል(የካርድ ክፍል ባለሙያወች እና ኡች አይቲ)	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3	4	4	3	3
14	የህሙማን ረዳት(ፖርተር)	1	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
15	የእስት ግንዘብ ሰብሳቢ	2	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3
16	የፅዳት ሰራተኛ	0	0	0	0	3	4	4	0	0	0	4	0	4	4	0
17	የአይን ህክምና ባለሙያ (ተኝቶ ህክምና በጀመሩተቋማት ብቻ)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	2	1	1
18	የስነ አምሮ ህክምና ባለሙያ(ተኝቶ ህክምና በጀመሩ ተቋማት ብቻ)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	2	1	1
	ጥርስ ህክምና ባለሙያ (አን	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1

	የባለሙያ አይነት	አለም ከተማ	አይራ	ደባርቅ	መሀል ሜዳ	ሸጋው ሞጣ	ከሚሴ	ተፈራ ሀይሉ	አትስታ	ፍኖተ ሰላም	ቅዱስ ላሊበላ	መተማ	እንጂባራ	ቦሩ	ኮምቦልቻ	መካለ ሰላም
20	የአምቡላንስ ሾፌር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
21	የሰርቪስ ሹፍር((ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
22	ኢመርጀንሲ ሜዲ ቴክኒሽያን	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
23	ኤሌክትሪሽያን /የውሀ ባለሙያ/ሁለገብ ጥገና	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
24	የእጥበት አገልግሎት(ላውንደሪ)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
25	ባዮሜዲካል ባለሙያ (ኦክስጅን ፕላንት በሌለባቸው የኦክስጅን ስራ ጨምሮ ይሰራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
26	ሰንተራል ስትራላይዜሽን ክፍል	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
27	በጤና ስርአት ማነቆ ተኮር ሪፎርም (SBFR)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
28	ዳይቴሽያን	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
29	አይ.ሲ.ቲ ባለሙያ /ኤች አይቲ/ ወረቀት አልባ አገልግሎት ለጀመሩ	2	0	0	0	0	2	0	2	0	0	0	0	2	2	2
30	የአንድ ማዕከል ሶታዊ ጥቃት አገልግሎት (GBV)		0	1	0	0	0	1	0	0	0	0	0	0	1	0
31	ፊዝዮትራፒ/አኮፒሽናል ቴራፒ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	
32	የአዲቲብል ፋርማሲ አካውንታንት(ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
33	የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪ (ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
34	የመድሀኒት ስቶር ባለሙያ(አን ኮል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1

የአጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች የትርፍ ሰዓት ስራ ተመዳቢዎች

	ሙያዎች	ወልድያ	ደሴ	ደብረ ታቦር	ደብረ ብርሀን	ደብረ ማርቆስ	ፈለገ ህይወት
	አይነት የሙያ እና የትምህርት ድጃ ያለ ነረስ	42	105	49	31	43	78
	ዋይፈሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	13	15	13	10	19	15
	ጠቅላላ ሀኪም	1	1	1	1	1	0
4	የተቀናጀ የቀዶ ህክምና አፈሰር	9	21	9	6	9	17
5	Dialysis unit(1 GP and 1 nurse)	0	2	0	0	0	2
6	አንስገርያ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	5	7	5	4	6	7
7	ፋርማሲ(በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	8	11	9	6	7	9
8	ክሊኒካል ፋርማሲ	2	4	2	2	2	4
9	ላቦራቶሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	10	12	10	8	10	12
10	የስነ ደዌ ላቦራቶረ ምርመራ ክፍል	1	1	1	1	1	1
11	Radiology – Technician	2	2	2	2	2	2
12	Radiology – Technologist	2	2	2	2	2	2
13	ላይዘን(የማህበራዊ አገልግሎት ስራ ደርቦ ይራል)	2	2	2	2	2	2
14	ካርድ ክፍል(የካርድ ክፍል ባለሙያወች እና ኤች አይቲ)	4	5	4	4	5	5
15	የህሙማን ሪዳት(ፖርተር)	4	8	4	4	4	8
16	የእለት ገንዘብ ሰብሳቢ	4	10	4	5	5	10
17	የአይን ህክምና ባለሙያ (ተኝቶ ህክምና በጀመሩ ተቋማት ብቻ)	1	1	1	1	1	1
18	የስነ አምሮ ህክምና ባለሙያ(ተኝቶ ህክምና በጀመሩ ተቋማት ብቻ)	2	2	2	2	2	2
19	የጥርስ ህክምና ባለሙያ (ኦን ኮል)	1	1	1	1	1	1
20	አምቡላንስ	1	1	1	1	1	1
21	ኢመርጀንሲ ሜዲ ቴክኒሽያን	1	1	1	1	1	1
22	ኤሌክትሪሽያን /የውሀ ባለሙያ/ሁለ ገብ ጥገና	2	2	2	2	2	2
23	የእጥበት አገልግሎት(ላውንደሪ)	2	2	2	2	2	2
24	የባዮሜዲካል ባለሙያ	1	1	1	1	1	1
25	የባእሜዲካል ባለሙያ አከስጅን ፕላንት ላላቸው	2	2	2	0	0	2
26	ሰንተራል ስትራላይዜሽን ክፍል	1	2	1	1	1	1
27	Cataract Surgeon	1	1	1	0	0	1
28	በጤና ስርአት ማነቆ ተኮር ሪፎርም (SBFR)	3	3	3	3	3	3
29	ዳይቴሽያን	1	1	1	1	1	1
30	Lab Aid	1	2	2	2	2	2
31	የሰርቪስ ሸፈር((ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	1	1	1	1	1	1
32	አይ.ሲ.ቲ ባለሙያ /ኤች አይቲ/ ወረቀት አልባ አገልግሎት ለጀመሩ	0	2	0	2	2	2
33	ፊዝዮትራፒ/አኮፔሽናል ቴራፒ	1	1	1	1	1	1
34	የአንድ ማዕከል ዶታዊ ጥቃት አገልግሎት (GBV)	1	1	1	1	1	1
35	የአዲቴብል ፋርማሲ አካውንታንት(ቅዳሜ፣እሁድና በዓላት ቀን)	1	1	1	1	1	1
36	የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪ/ኢንቫይሮንመታል ሄልዝ(ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	1	1	1	1	1	1
37	የሞርግ ሰራተኛ	1	1	1	1	1	1
38	የመድሀኒት ስቶር ባለሙያ(ኦን ኮል)	1	1	1	1	1	1
		136	239	145	115	145	204

CamScanner

	በደም ባንክ አገልግሎት			ቅዳሜ እሁድ እና በባላት ቀን የእሙትሪች አገልግሎት	
	የደም ባንክ ስም	አዳሪ ላብራቶሪ ባለሙያ	ቅዳሜ እሁድ እና በባላት ቀን ተቋሙ ላይ ዋይ(አንድ ነርስ ወይም ጤና መኮነን) እና አንድ ላብራቶሪ	እንደ አለም ጤና ድርጀት አንድ ቡድን 25 ዩኒት ደም ይሰበሰባል።	አንድ ቡድን 5 አባላት ይኖሩታል
1	ባህር ዳር	2	2	ሁለት ቡድን በየሳምንቱ	5
2	ጎንደር	2	2	እንድ ቡድን በየሳምንቱ	5
3	ደሴ	2	2	አንድ ቡድን በየሳምንቱ	5
4	ደብረ ማርቆስ	1	2	አንድ ቡድን በየሁለት ሳምንቱ	5
5	ደብረ ብርሀን	1	2	አንድ ቡድን በየሁለት ሳምንቱ	5
6	ደብረ ታቦር	1	2	አንድ ቡድን በየሁለት ሳምንቱ	5
7	ወልድያ	1	2	አንድ ቡድን ከሁለት ወር አንድ ቅዳሜና እሁድ ብቻ	5
8	ሰቆጣ	1	2	አንድ ቡድን ከሁለት ወር አንድ ቅዳሜና እሁድ ብቻ	5
9	መተማ	1	2	አንድ ቡድን ከሁለት ወር አንድ ቅዳሜና እሁድ ብቻ	5
10	ከሚሴ	1	2	አንድ ቡድን ከሁለት ወር አንድ ቅዳሜና እሁድ ብቻ	5
11	እንጅባራ	1	2	አንድ ቡድን ከሁለት ወር አንድ ቅዳሜና እሁድ ብቻ	5
12	ደባርቅ	1	2	አንድ ቡድን ከሁለት ወር አንድ ቅዳሜና እሁድ ብቻ	5
13	ፍኖተሰላም	1	2	አንድ ቡድን ከሁለት ወር አንድ ቅዳሜና እሁድ ብቻ	5
14	ድምር	15	26		65
	የማስታወሻ	በዋይ የሚመደበው የተንቀሳቃሽ ቡድን ሃላፊም መመደብ የሚችል ሲሆን የሚከፈለው ለውሉ ብቻ ነው			



CamScanner

		የጤና ጣቢያወች እና ጤና ኬላወች የተረኝነት ስምሪት መነሻ				
ተ ቁ	የጤና ጣቢያዉ ዓይነት	የከተማ ጤና ጣቢያ የቀዶ ህክምና እገልግሎት የሚሰጥ	የቀዶ ህክምና እገልግሎት የማይሰጥ የከተማ ጤና ጣቢያ	የገጠር ጤና ጣቢያ	አጠቃላይ ጤና ኬላ	
1	ጠቅላላ ሃኪም	1	1	1		
2	ጤና መኮንን	1	1	1		
3	ነርስ	4	3	1	1ነርስ/ጤና መኮንን	ሁሉም አይነት ነርስ/
4	ፋማሲ	2	1	1	1	አፒቲኤስ ለጀመሩ ሁለት ይሆናሉ ላልጀመሩ አንድ
5	ላብራቶሪ	2	1	1	1	
6	ሚድ ዋይፈሪ	2	2	2	1	
7	የጤና ኤክስቴሽን ባለሙያ /የቤተሰብ ጤና ፕሮፌሽናል	0	0	0	1	
8	ካርድ ከፍል	2	2	1	1	ሁለት ለተፈቀደላቸው 1 ኤች አይቲ እና አንድ ከኤች አይቲ ውጭ
9	IESO/ክሊኒካል ሚድዋይፍ	1	0	0		ሁለቱ በተራ ይሰራሉ በክሊኒካል ሚድዋይፍ የማይሸፈን ስራ ካለ IESO oncall ማስገባት ይቻላል
10	የስመመን ባለሙያ	1	0	0		
11	የአምቡላንስ ሹፌር	1	1	1		
12	ጽዳት	1	1	1		
13	የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ	1	1	1		
14	ፖርተር	1	1	1		ቅዳሜ እሁድ እና በባላት ቀን ብቻ
15	የእለት ገንዘብ ተቀባይ	1	1	1		
16	ድምር	21	16	11	6	



		የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የትርፍ ሰዓት ስራ ተመዳቢወች											
	የባለሙያ አይነት	እብናት	ቀራ	ባቲ	አዴት	አዲስ ዘመን	ጃዊ	መርጦ ለማሪያም	ነፋስ መውጫ	ወረታ	ጎንጂ ቆለላ	ዚገም	ለገሂዳ
1	በሁሉም አይነት የሙያ እና የትምህርት ድጃ ያለ ነረስ	9	6	12	16	17	8	10	8	12	6	6	6
2	ሚድዋይፈሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	4	3	4	7	5	7	5	5	6	2	2	2
3	ጠቅላላ ሀኪም	2	2	2	3	3	2	2	2	2	2	2	2
4	የተቀናጀ የቀዶ ህክምና አፊሰር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
5	አንስገርያ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
6	Pharmacy(በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	3	3	2	2	2	2	2	2	2
7	ክሊኒካል ፋርማሲ	0	0	1	1	1	1	0	0	0	0	0	0
8	ላቦራቶሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	3	4	4	2	2	2	3	2	2	2
9	Radiology – Technician	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
10	Radiology – Technologist	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
11	ላይዘን(የማህበራዊ አገልግሎት ስራ ደርቦ ይራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
12	ካርድ ክፍል(የካርድ ክፍል ባለሙያወች እና ኤች አይቲ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
13	የህሙማን ረዳት(ፖርተር)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
14	የእለት ገንዘብ ሰብሳቢ	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
15	የፅዳት ሰራተኛ	3	3	3	0	3	3	3	3	3	3	3	3
16	የአይን ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
17	የስነ ዓምሮ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
18	የጥርስ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
19	የአምቡላንስ ሾፌር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
20	ኢመርጀንሲ ሜዲ ቴክኒሽያን(EMT)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
21	ኤሌክትሪሽያን /የውሀ ባለሙያ/ሁለ ገብ ጥገና	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
22	የእጥበት አገልግሎት(ላውንደሪ)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
23	ባዩሜዲካል ባለሙያ (አክሰጅን ፕላንት በሌለባቸው የአክሰጅን ስራ ጨምሮ ይሰራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
24	በጤና ስርአት ማነቆ ተኮር ሪፎርም (SBFR)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
25	የኦዲቲበል ፋርማሲ አካውንታንት(ቅዳሜ፤እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	0	0	0
26	የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪ ቅዳሜ፤እሁድና በህዝብ በዓላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1

CamScanner

		የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የትርፍ ሰዓት ስራ ተመዳቢወች										
	የባለሙያ አይነት	ደብረ ሲና	መቅደላ	ወረኢሉ	አረርቲ	አማራ ሳይንት	አዲስ አለም	ወግዲ	ቢቡኝ	የጁቢ	መካነ እየሱስ	ዳንግላ
1	በሁሉም አይነት የሙያ እና የትምህርት ድጃ ያለ ነረስ	8	9	7	10	7	18	6	6	7	8	10
2	ሚድዋይፈሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	4	2	5	2	12	4	4	3	5	7
3	ጠቅላላ ሀኪም	2	2	2	2	2	4	2	2	2	2	2
4	የተቀናጀ የቀዶ ህክምና አፊሰር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
5	አንስዝርያ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
6	Pharmacy(በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	3	2	2	2	2	2
7	ክሊኒካል ፋርማሲ	0	0	0	1	0	1	0	0	0	0	1
8	ላቦራቶሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	3	2	4	2	2	2	2	3
9	Radiology – Technician	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
10	Radiology – Technologist	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
11	ላይዘን(የማህበራዊ አገልግሎት ስራ ደርቦ ይራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
12	ካርድ ክፍል(የካርድ ክፍል ባለሙያወች እና ኤች አይቲ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
13	የህሙማን ረዳት(ፖርተር)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
14	የእለት ገንዘብ ሰብሳቢ	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
15	የፅዳት ሰራተኛ	3	3	3	0	3	0	3	3	3	3	3
16	የአይን ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
17	የስነ ዓምሮ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
18	የጥርስ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
19	የአምቡላንስ ሸፈር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
20	ኢመርጀንሲ ሜዲ ቴክኒሽያን(EMT)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
21	ኤሌክትሪሽያን /የውሀ ባለሙያ/ሁለ ገብ ጥገና	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
22	የእጥበት አገልግሎት(ላውንደሪ)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
23	ባዮሜዲካል ባለሙያ (ኦክስጅን ፕላንት በሌለባቸው የኦክስጅን ስራ ጨምሮ ይሰራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
24	በጤና ስርአት ማኔቆ ተኮር ሪፎርም (SBFR)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
25	የኦዲቴበል ፋርማሲ አካውንታንት(ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
26	የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪ ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ በዓላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1

CamScanner

		የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የትርፍ ሰዓት ስራ ተመዳቢወች										
	የባለሙያ አይነት	ደብረ ኤሊያስ	ዝቀላ	ዳባት	ደንቢያ	አብርሀ ጂራ	አንበሳሜ	ቢቸና	ደብረ ወርቅ	ወገዳ	ሀይቅ	ጹርቤቱ
1	በሁሉም አይነት የሙያ እና የትምህርት ድጃ ያለ ነረስ	8	5	5	10	6	8	11	8	8	8	12
2	ሚድዋይፈሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	5	2	3	5	3	4	6	4	4	3	5
3	ጠቅላላ ሀኪም	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
4	የተቀናጀ የቀዶ ህክምና አፈሰር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
5	አንስጥሪያ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
6	Pharmacy(በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
7	ክሊኒካል ፋርማሲ	0	0	0	1	0	0	1	0	0	0	0
8	ላቦራቶሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	3
9	Radiology – Technician	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
10	Radiology – Technologist	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
11	ላይዘን(የማህበራዊ አገልግሎት ስራ ደርቦ ይራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
12	ካርድ ክፍል(የካርድ ክፍል ባለሙያወች እና ኤች አይቲ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
13	የህሙማን ረዳት(ፖርተር)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
14	የእለት ገንዘብ ሰብሳቢ	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
15	የፅዳት ሰራተኛ	3	3	3	3	3	3	0	3	3	3	3
16	የአይን ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
17	የስነ ዓምሮ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
18	የጥርስ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
19	የአምቡላንስ ሸፌር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
20	ኢመርጀንሲ ሜዲ ቴክኒሽያን(EMT)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
21	ኤሌክትሪሽያን /የውሀ ባለሙያ/ሁለ ገብ ጥገና	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
22	የእጥበት አገልግሎት(ላውንደሪ)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
23	ባዩሚዲካል ባለሙያ (አክሰጅን ፕላንት በሌለባቸው የአክሰጅን ስራ ጨምሮ ይሰራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
24	በጤና ስርአት ማነቆ ተኮር ሪፎርም (SBFR)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
25	የኦዲቲብል ፋርማሲ አካውንታንት(ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
26	የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪ ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ በዓላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1

CamScanner

		የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የትርፍ ሰዓት ስራ ተመዳቢዎች											
	የባለሙያ አይነት	ሽድሆ መቂት	ደጀን	ሳንጃ	አይከል	ቡሬ	አርባያ	አምደ ወርቅ	ማክሰኝት	ደላንታ	ፈረስ ቤት	ከለላ	ተንታ
1	በሁሉም አይነት የሙያ እና የትምህርት ድጃ ያለ ነረስ	7	9	13	13	11	10	4	6	8	5	7	4
2	ሚድዋይፈሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	4	4	5	7	4	2	4	3	3	3	2
3	ጠቅላላ ሀኪም	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
4	የተቀናጀ የቀዶ ህክምና አፈሰር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
5	አንስዝያ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
6	Pharmacy(በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
7	ክሊኒካል ፋርማሲ	0	0	1	1	1	1	0	0	0	0	0	0
8	ላቦራቶሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	3	3	3	3	2	2	2	2	2	2
9	Radiology – Technician	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
10	Radiology – Technologist	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
11	ላይዘን(የማህበራዊ አገልግሎት ስራ ደርቦ ይራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
12	ካርድ ክፍል(የካርድ ክፍል ባለሙያወች እና ኤች አይቲ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
13	የህሙማን ረዳት(ፖርተር)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
14	የእለት ገንዘብ ሰብሳቢ	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
15	የፅዳት ሰራተኛ	3	0	3	3	0	3	3	3	3	3	3	3
16	የአይን ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
17	የስነ ዓምሮ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
18	የጥርስ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
19	የአምቡላንስ ሾፌር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
20	ኢመርጀንሲ ሜዲ ቴክኒሽያን(EMT)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
21	ኤሌክትሪሽያን /የውሀ ባለሙያ/ሁለ ገብ ጥገና	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
22	የእጥበት አገልግሎት(ላውንደሪ)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
23	ባዩሜዲካል ባለሙያ (አክስጅን ፕላንት በሌለባቸው የአክስጅን ስራ ጨምሮ ይሰራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
24	በጤና ስርአት ማነቆ ተኮር ሪፎርም (SBFR)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
25	የኦዲቲብል ፋርማሲ አካውንታንት(ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	1	1	1	1	1	0	1	0	1	1	1	1
26	የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪ ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ በዓላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1

CamScanner

		የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የትርፍ ሰዓት ስራ ተመዳቢወች											
	የባለሙያ አይነት	ታች ጋይንት	ሽበል በረንታ	ወገራ	ሉማሚ	አንዳቢት	ጨፋ ሮቢት	ሞላሌ	ግምጃ ቤት	መርሳ	ቻግኒ	አጣየ	ሚዳ ወረሞ
1	በሁሉም አይነት የሙያ እና የትምህርት ድጃ ያለ ነረስ	6	5	4	12	7	5	6	12	11	23	10	4
2	ሚድዋይፈሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	3	3	3	5	3	2	3	6	4	8	5	2
3	ጠቅላላ ሀኪም	2	2	2	2	2	2	2	2	2	4	2	2
4	የተቀናጀ የቀዶ ህክምና ኦፊሰር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
5	አንሰገርያ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
6	Pharmacy(በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	3	2	2
7	ክሊኒካል ፋርማሲ	0	0	0	0	0	0	0	1	1	1	1	0
8	ላቦራቶሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	3	2	2	2	3	3	4	2	2
9	Radiology – Technician	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
10	Radiology – Technologist	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
11	ላይዘን(የማህበራዊ አገልግሎት ስራ ደርቦ ይራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
12	ካርድ ክፍል(የካርድ ክፍል ባለሙያወች እና ኤች አይቲ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
13	የህሙማን ረዳት(ፖርተር)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
14	የእለት ገንዘብ ሰብሳቢ	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
15	የፅዳት ሰራተኛ	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3	0	3
16	የአይን ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
17	የስነ ዓምሮ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
18	የጥርስ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
19	የአምቡላንስ ሸፌር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
20	ኢመርጀንሲ ሜዲ ቴክኒሽያን(EMT)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
21	ኤሌክትሪሽያን /የውሀ ባለሙያ/ሁለ ገብ ጥገና	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
22	የእጥበት አገልግሎት(ላውንደሪ)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
23	ባዩሜዲካል ባለሙያ (አክስጅን ፕላንት በሌለባቸው የአክስጅን ስራ ጨምሮ ይሰራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
24	በጤና ስርአት ማነቆ ተኮር ሪፎርም (SBFR)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
25	የኦዲቲብል ፋርማሲ አካውንታንት(ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
26	የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪ ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ በዓላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1

CamScanner

		የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የትርፍ ሰዓት ስራ ተመዳቢወች												
	የባለሙያ አይነት	ሸሁራ	ሸዋሮቢት	ደነባ	ዋድላ	ጎሀላ	ደምበጫ	ደልጊ	ጠገዴ	ቆቦ	ጃናሞራ	ጃማ	ሊበን	መራዊ
1	በሁሉም አይነት የሙያ እና የትምህርት ድጃ ያለ ነረስ	8	12	7	7	6	8	10	4	11	5	8	10	20
2	ሚድዋይፈሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	5	5	2	2	3	5	5	2	5	3	3	5	9
3	ጠቅላላ ሀኪም	2	2	2	2	2	2	2	1	2	2	2	2	4
4	የተቀናጀ የቀዶ ህክምና አፊሰር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
5	አንሰገርያ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
6	Pharmacy(በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	1	2	2	2	2	3
7	ክሊኒካል ፋርማሲ	0	1	0	0	0	0	1	0	0	0	0	0	1
8	ላቦራቶሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	3	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	4
9	Radiology – Technician	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
10	Radiology – Technologist	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
11	ላይዘን(የማህበራዊ አገልግሎት ስራ ደርቦ ይራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
12	ካርድ ክፍል(የካርድ ክፍል ባለሙያወች እና ኤች አይቲ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
13	የህሙማን ረዳት(ፖርተር)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
14	የእለት ገንዘብ ሰብሳቢ	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
15	የፅዳት ሰራተኛ	3	0	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3
16	የአይን ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
17	የስነ ዓምሮ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
18	የጥርስ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
19	የአምቡላንስ ሸፈር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
20	ኢመርጀንሲ ሜዲ ቴክኒሽያን(EMT)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
21	ኤሌክትሪሽያን /የውሀ ባለሙያ/ሁለ ገብ ጥገና	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
22	የእጥበት አገልግሎት(ላውንደሪ)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
23	ባዩሜዲካል ባለሙያ (ኦክስጅን ፕላንት በሌለባቸው የኦክስጅን ስራ ጨምሮ ይሰራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
24	በጤና ስርአት ማነቆ ተኮር ሪፎርም (SBFR)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
25	የኦዲቴብል ፋርማሲ አካውንታንት(ቅዳሜ፤እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	0	1	1	1	0	1	1	0	1	1	1	1	1
26	የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪ ቅዳሜ፤እሁድና በህዝብ በዓላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1

CamScanner

		የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የተርፍ ሰዓት ስራ ተመጸዚወች												
	የባለሙያ አይነት	ሽሁራ	ሸዋሮቢት	ደነባ	ሞጁላ	ጎሀላ	ደምበጫ	ደልጊ	ጠገዴ	ቶበ	ጃናሞራ	ጃማ	ሊበን	መራዊ
1	በሁሉም አይነት የሙያ እና የትምህርት ደረጃ ያለ ነረስ	8	12	7	7	6	8	10	4	11	5	8	10	20
2	ሚድዋይፈሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	5	5	2	2	3	5	5	2	5	3	3	5	9
3	ጠቅላላ ሀኪም	2	2	2	2	2	2	2	1	2	2	2	2	4
4	የተቀናጀ የቀዶ ህክምና አፈሰር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
5	አንስዝያ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
6	Pharmacy(በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	2	2	2	2	2	2	1	2	2	2	2	3
7	ክሊኒካል ፋርማሲ.	0	1	0	0	0	0	1	0	0	0	0	0	1
8	ላቦራቶሪ (በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያሉ)	2	3	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	4
9	Radiology – Technician	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
10	Radiology – Technologist	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
11	ሳይዘን(የማህበራዊ አገልግሎት ስራ ደርቦ ይራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
12	ካርድ ክፍል(የካርድ ክፍል ባለሙያወች እና ኤች አይቲ)	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
13	የህሙማን ረዳት(ፖርተር)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
14	የእለት ገንዘብ ሰብሳቢ.	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2	2
15	የፅዳት ሰራተኛ	3	0	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3	3
16	የአይን ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
17	የስነ ዓምሮ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
18	የጥርስ ህክምና ባለሙያ	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
19	የአምቡላንስ ሾፈር	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
20	ኢመርጀንሲ ሜዲ ቴክኒሽያን(EMT)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
21	ኤሌክትሪሽያን /የውሀ ባለሙያ/ሁለ ገብ ጥገና	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
22	የእጥበት አገልግሎት(ላውንደሪ)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
23	ባዩሜዲካል ባለሙያ (አክሰጅን ፕላንት በሌለባቸው የአክሰጅን ስራ ጨምሮ ይሰራል)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
24	በጤና ስርአት ማነቆ ተኮር ሪፎርም (SBFR)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1
25	የኦዲቴብል ፋርማሲ አካውንታንት(ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ ባአላት ቀን)	0	1	1	1	0	1	1	0	1	1	1	1	1
26	የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪ ቅዳሜ፣እሁድና በህዝብ በዓላት ቀን)	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1	1

CamScanner

ተጨማሪ ማብራሪያ

በመመሪያው የተገለፀው እና የተመላከተው የትርፍ ሰአት ስራ የሚመደበው የስምሪት ቁጥር እንደተጠበቀ ሆኖ ለአተገባበር ያመች ዘንድ ማብርሪያ የሚያስፈልጋቸው እንደሚከተሉት ተርበዋል ።

1. የትርፍ ሰአት ስራ ስምሪት ለባለሙያ የሚከፋፈል ጥቅማ ጥቅም ሳይሆን የማይቋረጥ የህክምና አገልግሎትን ለማስቀጠል የሚሰጥ የስራ ስምሪት ሲሆን እንደ መብት የትርፍ ሰዓት ስራ ልስራ ብሎ መጠየቅ አይቻልም፤በተረኝነት እንዲሰሩ የተፈቀዱትም ስምሪት መሰጠት እና መከፈል ያለበት ስራ ሲሰራ ብቻ ነው ፤ለምሳሌ ራዲዮሎጂ ላይ የተመደቡ ባለሙያወች የራጅ ማሽን ከሌለ ወይም ከተበላሸ የተረኝነት ክፍያ አይከፈልም ሌሎችም በተመሳሳይ የተሰጡ ስምሪቶች ስራ እስካለ ብቻ የሚሰጥ ስምሪት እና የሚከፈል መሆኑ ታውቆ ተግባራዊ እንዲደረግ፤
2. የተኙቶ ህክምና በሌለበት በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የተመደቡ የስነ አምሮ ባለሙያወች፤የአይን እና የጥርስ ህክምና ባለሙያወች በመመሪያው መሰረት በ On call ስምሪት እንዲሰጣቸው፤የተኙቶ ህክምና ባለባቸው ጠቅላላ እና አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ደግሞ የተረኝነት ስምሪት ይሰጣቸዋል።
3. በትርፍ ሰአት ስምሪት (Midwife,Nurse ,Psychiatry,& Anesthesia፤Laboratory etc..) እና ሌሎችም ባለሙያች ማለት በዲፕሎማ ፣ በዲግሪ እና 2ኛ ዲግሪ ታሳቢ ያደረገ ነው ።
4. የነርስ እና የጠቅላላ ሀኪም እጥረት ባለባቸው ተቋማት ላይ ጤና መኮነን ባለሙያዎች በመደበኛ የስራ ቀን ተመድበው እየሰሩ ከሆነ የትርፍ ሰአት ስምሪቱን በመደበኛ የስራ ቀን በሚሰሩበ ክፍል በትርፍ ሰአት ስምሪት የሚሰጣቸው ሲሆን በተረኝነት ከተሰጠው ቁጥር ጋር ታሳቢ ተደርጎ ይሰጣቸዋል።ምሳሌ፦በመደበኛ ሰአት የነርስ ስራ ከሸፈኑ ሆስፒታሉ በነርስ ቁጥር የትርፍ ሰአት ስምሪት አካል አድርጎ መውሰድ እና የህክም ስራ ከሸፈኑ ለህክም በተሰጠው ስምሪት መሆን አለበት፤
5. በጠቅላላ ሆስፒታል ካርድ ክፍል ላይ ከተመደቡ 02 ሰራተኞች ውጭ የሁመማን መረጃ ወደ ኮምፒውተር የሚመዘግብ አንድ የመረጃ ባለሙያ ተመድቦ ይሰራል። በመጀመሪያ ደረጃ ሆሲፒታል ለካርድ ክፍል ከተመደቡት መካከል አንደኛ በቋሚነት የመረጃ በለሙያ ሆኖ



አንዲሰራ ይደረጋል፤ይህ ስምሪት በሌሎች ክፍሎች ተመድበው የሚሰሩ የመረጃ ባለሙያዎችን አይመለከትም ::

6. ሆስፒታሎች በጤና ስርአት ማነቆ ተኮር ማሻሻያ መርሀ ግብር ትግበራ የሚከታተሉ የአገልግሎት ጥራት ቁጥጥር አስተባባሪአና ባለሙያዎች፤እቅድ አስተባባሪ፤ሜዲካል ዳይሬክተር፤ስራ አስኪያጅ፤ላቦራቶሪ አስተባባሪ፤ፋርማሲ አስተባባሪ፤ ዋና ሜትረን፤ የሰው ሀብት ቡድን መሪ እና የግኝር ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ) መካከል በአጠቃላይ ስፔሻላይዝድ 3 በጠቅላላ 2 እና በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች 1 በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት እየተመደቡ ተግባራቱን በየቀኑ እንዲከታተሉ ይደረጋል።

7. አንድ እና ሁለት ተመዳቢ ባለሙያዎች በሚኖርበት ጊዜ የጤና ስራ ከህይወት ጋር የተያያዘ እና የማይቋረጥ በመሆኑ ከ212 ሰዓት በላይ መድቦ ማሰራት የሚቻል ሲሆን የሚሰሩ ባለሙያዎች ከ212 ሰዓት በላይ ስለመስራታቸው ከላይ በተራ ቁጥር 6 የተቀመጠውን ስርዓት በመጠቀም በሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር እና ስራ አስኪያጅ ማረጋገጭ እየተሰጠበት ብቻ ይሆናል፤ማለትም ከ212 ሰዓት በላይ ለህሙማን አገልግሎት ስለመሰጠቱ እና ታካሚ መኖሩ እየተረጋገጠ የሚስተናገድ ሲሆን የሚሰሩት ወይም የሰሩት ስራ ሳይኖር አንድ ወይም ሁለት ስለሆኑ ብቻ ከተቀመጠው ሰዓት በላይ መክፈል ግን አይቻልም።

8. የመጀመሪያ ደረጃ ህክምናን ለማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት በጤና ጣቢያዎች እና በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የድንገተኛ ቀዶ ህክምና ኦፊሰሮች(IESO መመደብ አስፈላጊ ነው። ይሁን እንጂ በጠቅላላ ሆስፒታሎች እና በአጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች የተመደቡት የድንገተኛ ቀዶ ህክምና ኦፊሰሮች (IESO) ለአሁኑ ባሉበት ስምሪት የሚሰጣቸው ሲሆን በቀጣይ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ተቋማት እየገቡ ሲሄዱ በሁለተኛ እና 3ኛ ደረጃ ህክምና ተቋማት በክፍት ቦታ አይተካባቸውም ::

9. የቀዶ ህክምና ስራ የሚሰሩ ስፔሻሊስት ሀኪሞች ቁጥር 2 እና በላይ ባሉባቸው በሁሉም ደረጃ የሚገኙ ሆስፒታሎች እንዲሁም ስፔሻሊስት ሀኪሞች ኖረው IESO ባለሙያዎች በመመሪያው መሰረት ከ212 ሰአት በላይ የትርፍ ሰአት ስራ ስምሪት መስጠት እና ክፍያ መክፈል አይቻልም።

10. ጤና ተቋማትን ላይ የጅን እና ሳኒቴሽን ቁጥጥር ስራ ቀጣይነት ባለው አግባብ እንዲሰራ እና ተቋዉሙን ብክለት ለመከላከል ከሰኞ እስከ አርብ የሚደረገው የአከባቢ ጤና ተቆጣጣሪዎችን ስራ በሳምንቱ የረፍት ቀናትም ለማስቀጠል ቅዳሜ፥ እሁድ እና በህዝብ በአላት ቀን ለቀን ብቻ ስምሪት የሚሰጣቸው ይሆናል።